በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 196346
?? 26/11/2013 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - አቶ በፍቃዱ ጌታቸው፡- **ጠበቃ ከፋለኝ ደጉ ቀረቡ**

ተጠሪ - 1. አቶ ዮናስ ጌታነህ 2. ወ/ሮ ብዙነሽ ጌታነህ 3. አቶ ተስፋዬ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሸዋዬ ጌታነህ 5. ወ/ሮ ዘነበች ጌታነህ 6. ወ/ሮ ሙሉ ብርሃን ጌታነህ
7. አቶ በየነ ደረሰ 8. አቶ አዲሱ ጌታነህ ፡- **ተወካይ ዘነበች ጌታነህ ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 22 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 182644 ሰኔ 12 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ያከራከረን ቤት በእናቴ ስም የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ጣልቃ ገብዎች ቤቶቹን ሰራን የሚሉት 1ኛ ጣ/ገብ አያቴ ሞግዚቴ ሆኖ ባለበት ጊዜ መሆኑ እየታወቀ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያላደረኩትን እርቅ መሰረት አደርጎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ እናቴ ወ/ሮ ዓለምነሽ ጌታነህ በ1989 ዓ/ም ሞታለች፡፡

ወራሽነቱን በ2009 ዓ/ም አረጋግጫለሁ፡፡ እናቴ በህይወት እያለች ያፈራችው ንብረት በን/ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ውስጥ ያለ የቤት ቁጥር 1711 የሆነው ቤት የእናቴ ውርስ ሀብት ስለሆነና አጣርቼ ያቀረብኩት በመሆኑ እንዲጸድቅልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ጣልቃ ገብዎች 1. አቶ ጌትነት አበበ፣ 2. አቶ ዮናስ ጌትነት፣ 3. ብዙነሽ ጌታነህ፣ 4. አቶ ተስፋዬ ጌታነህ 5. ሸዋዬ ጌታነህ 6. ዘነበች ጌታነህ 7. ሙሉብርሃን ጌታነህ 8. ፊቴን በየነ 9. አቶ አዲሱ ጌታነህ ባቀረቡት አቤቱታ ቤቱ በሚች ወ/ሮ ዓለምነሽ ጌታነህ ስም ይመዝገብ እንጂ ቦታው ላይ ያሉት ቤቶች በጣልቃ ገብዎች የተሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም አቤቱታው ውድቅ ይሁንልን በሚል ተከራክረዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 124770 ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ያከራከረው የቤት ቁጥር 1171 የሆነው ቤት ቦታው በአመልካች እናት ስም የተመዘገበ መሆኑን በቀረበው የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም በቦታው ላይ ጣልቃ ገብዎች ቤት የሰሩበትና ሲኖሩበት የነበሩ መሆኑን፣ ቤቱን ሲሰሩ የተቃወማቸው የሌለ መሆኑ በመረጋገጡና አመልካችም ያላስተባበለው በመሆኑ፣ የንብረት ባለቤት ነኝ የሚል በሀብቱ በገንዘቡ በዕውቀቱ ያፈራው ንብረት መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባውና ይህንንም አመልካች ባለማረጋገጡ የውርስ ንብረት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ አከራክሮ በመ/ቁጥር 222293 ሐምሌ 4 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ያከራከረው የቤት ቁጥር 1171 የሆነው ቤት በአመልካች እናት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑና እናቴ ስትሞት 1ኛ ጣልቃ ገብ አያቱ የአመልካች ሞግዚት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ 1ኛ ጣልቃ ገብ የአመልካች ሞግዚት ሆኖ ሀብቱንም ቁጭር ሲያስተዳድር ባለበት ጊዜ ከ2ኛ እስከ 9ኛ ያሉት ጣልቃ ገብዎች በቦታው ላይ ቤት በመስራታቸው የተቃወማቸው የለም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ቤቱ የውርስ ንብረት ነው፡፡ ጣልቃ ገብዎች ሰራን ለሚሉት ቤት ግምቱን መጠየቅ ይችላሉ ሲል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ወስኗል፡፡ ጣልቃ ገብዎች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው አከራክሮ በመ/ቁጥር 182644 ሰኔ 12 ቅን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ያከራከረው የቤት ቁጥር 1171 የሆነው ቤት በአመልካች እናት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም ይዞታውን ያገኙት 1ኛ ጣልቃ ገብ አባቷ ናቸው፡፡ በጊዜው አባቷ 1ኛ ጣልቃ ገብ ሌላ ቤት ስለነበረው በአመልካች እናት (በልጁ) ስም ያስመዘገበ መሆኑና በይዞታው ላይ ቤቶች የተሰሩትም በጣልቃ ገብዎች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ግራ ቀኙ በ30/8/2002 ዓ/ም በሽማግሌዎች ባደረጉት እርቅ ይህንኑ ፍሬ ነገር በማስፈር ጣልቃ ገብዎች የሰሩት ቤት የራሳቸው ሆኖ አመልካች የሰራውን 9*16 = 144 ካ/ሜ ይዞታ እንዲወስድ የተስማሙ መሆኑንም ያሳያል፡፡ ይሁንና አመልካች የእርቁ የመጀመሪያ ገጽ ላይ አልፈረምኩም፣ ሽማግሌዎች በመጨረሻው ገጽ ላይ አልፈረሙም ከሚል ክርክር ውጪ እርቁን አላደረኩም የሚል ክርክር የለውም፡፡ በዚሁ እርቅ መሰረት መፈጸም ሲገባ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሞግዚትነቱን ሁኔታ ብቻ በማየት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው ሲል የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤትና ይዞታ በአሁኑ አመልካች እናት ስም ተመዝግቦ እያለ የውርስ ሃብት አይደለም ተብሎ ለተጠሪዎች የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ታህሳስ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልን ሲሉ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን

የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙን ያከራከረው ቤት በአሁን አመልካች እናት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ ቤቱ በአሁን አመልካች እናት ስም የተመዘገበው በተለያየ ምክንያት ከቦታቸው ለተነሱ ነዋሪዎች መንግስት ምትክ ቦታ ሲሰጣቸው ለስር ፍ/ቤት 1ኛ ጣልቃ ገብ የተሰጠና 1ኛ ጣልቃ ገብ ሌላ ቤት ስለነበረውና በወቅቱ ለከተማው ነዋሪ ሁለት ቤት ስለማይፈቀድ በልጁ በአሁን አመልካች እናት ስም ያስመዘገበ መሆኑን፣ እንዲሁም በይዘታው ላይ ያሉት ቤቶች በጣልቃ ገብዎች የተሰሩ መሆኑንም ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት አረጋግጦ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች አቤቱታ ቅሬታ ያከራከረው ቤት የውርስ ንብረት መሆኑ በቀረቡት ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ አቤቱታዬ ውድቅ መሆኑ ተገቢ አይደለም የሚል የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1) መሰረት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 182644 ሰኔ 12 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻላሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም